# የጥሩዬ እምባ




ወረደ በውስጣችን፥ ተንቆረቆረ ያሴት እምባ
ተቤጂንግ አምባ እምብርት፥ የጀግኒቷ እውን ጠባ፤
ወረደ ታንጀታችን፥ የጥሩዬ ላብ ወለላ
የምዬ ፍቅር ተምሳሌት፥ ተዚያች ትንሽ አለላ፤
ወረደ ተንቆረቆረ፥ አካል ገላን አማክሎ
ጥሩዬ መሠረት ቢሉ፥ አብዬንስ ማን አክሎ?
ተኃይሌ ተቀነኒሳ፥ ተስለሺ ተውሎ
ምነው አይሌቅ፥ ዓለምን ተኋላ ጥሎ?!
ይሌቃል እጂ፥ ይበልጡታል አሳምሮ
የጠቢያ ልጅ ቁርጠኛ ነው፥ ተተያዘለት ቀጠሮ፤

እናም ጥሩዬ... የምባሽ ሙቀት ደርሶናል
እኛን አሙቀሽ... ድፍን ዓለምን ደንቀሻል፤
አምስት አሥር ሺ ጨርግደሽ፥
        በወርቅ አልማዝ ተጊጠሻል
ሙሽራችን ታይን ያውጣሽ፥
        እምባሽን በልባችን አብሰናል
ጨጉላሽ አብቧልን እያዜምን፥
        መልካም ፍጥምጥም ብለናል፤

- በአበራ ለማ

(ሳርፕስቦርግ፥ ኖርዌይ፣ ሰዓት 15፡00፣ 22.08.08)